# ወረተኛው ጊዜ

አብርሃም በየነ

አዳፋ ነው ልብሱ

ድንጊያ ነው ትራሱ

ለእግሩ ጫማ የለው

መርዝ ነው ምላሱ

ለሚሉት አማራ

ድህነት አውርሰው

ለእግሩ ጫማ የለው

ይሉታል መልሰው።

እነ ግፍ አይፈሬ ዘመናይ ባለ ቀን

ሲመጻደቁበት በድሃው ሰቀቀን

ወረቱን ዘራርፈው ከቀየው አፍልሰው

መርዝ ነው ምላሱ ይሉታል መልሰው።

የናንተው ብርሃን የኛው ቀን ጨልሞ

ለጊዜው ቢመስልም የሚቆይ ለከርሞ

ግን ይኸ ቀን አልፎ ሌላ ቀን ሲመጣ

ያገላብጠናል እንደ ምጣድ ቂጣ።

ጥር 2006